# የኅብረት ሥራ ማኅበራት አደረጃጀትና ልዩ ባሕርያት

በአገራችን የኅብረት ሥራ ማኅበራት ለመጀመሪያ ጊዜ የተደራጁት ከ50 ዓመታት በፊት በገበሬዎች የእርሻ ኅብረት ሥራ ድንጋጌ ቁጥር 44/1953 ሲሆን፣ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ አዋጆችና ደንቦች ወጥተዋል፡፡ የእነዚህ አዋጆች ይዘት በየጊዜው መንግሥታቱ ይከተሉት የነበሩትን ርዕየተ ዓለማዊ ባህሪያትን አንፀባርቀዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት የኅብረት ሥራ ማኅበራት በፌዴራል ደረጃ በአዋጅ ቁጥር 147/1991፣ እና በማሻሻያው አዋጅ ቁጥር 402/1996 እንዲሁም በደንብ ቁጥር 106/1996 መሠረት የተደራጁ ሲሆን፣ ክልሎችም የየራሳቸውን አዋጆች ቀርጸዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት የኅብረት ሥራ ማኅበራት በተለያዩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ በመሳተፍ ለአባሎቻቸውና ለጠቅላላው ኅብረተሰብ የራሳቸውን አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ በዚህ ጽሑፍ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን የሚገዛውን አዋጅ መሠረት በማድረግ አደረጃጀታቸውና ልዩ ባሕርያቸውን በአጭሩ እንመለከታለን፡፡

## የኅብረት ሥራ ማኅበር ትርጉምና ባህርያት

የኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 (ከዚህ በኋላ አዋጅ እየተባለ የሚጠራው) በአንቀጽ 2(2) ‹‹የኅብረት ሥራ ማኅበር›› ማለት ‹‹ሰዎች በፈቃደኝነት ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮቻቸውን በጋራ ለመፍታት የሚያቋቁሙትና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚያስተዳድሩት ማኅበር ነው፡፡›› በሚል ትርጉም ይሰጣል፡፡ ይህ ትርጓሜ የአለም ዓቀፍ የኅብረት ሥራ ኅብረት (International cooperative alliance) ከሰጠው ትርጉም አኳያ ጠባብ ቢሆንም፣ መሠረታዊ የሆነውን ፈቃደኝነትና በዲሞክራሲያዊ መንገድ መተዳደርን በማካተቱ በጎ ጎን አለው፡፡ እ.ኤ.አ. በ1995 በአለም ዓቀፍ ኅብረት የተሰጠው ትርጉም የኅብረት ሥራ ማኅበራት የአባላትን የባህላዊና መንፈሳዊ ፍላጐት ለማሟላት ሲባልም ሊደራጁ እንደሚችሉ ያሳያል፡፡ በእኛ ሕግ ግን ማኅበራት ከማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ያለፈ ድርሻ የላቸውም፡፡

የኅብረት ሥራ ማኅበራት ከበጎ አድራጐት ድርጅቶችም ሆነ ከንግድ ማኅበራት የሚለዩበት ባህርያት አሏቸው፡፡ ቀዳሚው መለያ ዓላማ ነው፡፡

የኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚቋቋሙበት ዓላማ የአባላትን ተመሳሳይ ፍላጐት በአነስተኛ ወጪ ለማሟላት እንጂ ለአባላት ትርፍ ለማስገኘት አይደለም፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 4 የኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚቋቋሙበትን ዓላማዎች የዘረዘረ ሲሆን፣ በዝርዝሩ ውስጥ ለአባላት ትርፍ ለማስገኘት በሚያስችል ሥራ እንደሚሳተፉ አይገልፅም፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 35፣ አንድ ማኅበር ለአባላት ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመ ሌላ ማኅበር ካልሆነ በቀር ብድር መስጠት እንደማይችል መደንገጉም ለዚህ ነው፡፡ በተግባር ግን አንዳንድ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ለአባሎቻቸው ከሚሰጡት አገልግሎት ባለፈ አባል ካልሆኑ ግለሰቦች ጋር የንግድ ልውውጥ ሲያደርጉ ይስተዋላል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ማኅበራቱ ከሌሎች የንግድ ማኅበራት ጋር ያላቸውን ልዩነት ለማስተዋል ያስቸግራል፡፡

በንግድ ከመሳተፍ አንፃር በተግባር የሚነሳው አከራካሪ ነጥብ፣ ማኅበራት የሚያበድሩት ብድር የወለድ መጠንን የሚመለከት ነው፡፡ አዋጁ በአንቀጽ 34(1) ማኅበራት ስለሚበደሩት ብድር፣ በአንቀጽ 34(2) ደግሞ አበድረው ስለሚቀበሉት የወለድ መጠን ይደነግጋል፡፡ በ34(2) መሠረት ማኅበሩ

የሚያገኘው ወለድ ከባንክ የመበደሪያ ወለድ ሊበልጥ አይችልም የሚል ሲሆን፣ በአዋጅ ቁጥር 402/96 እንዲሠረዝ ተደርጓል፡፡ በማሻሻያው የመሠረዙ ውጤት ግን አከራካሪ ሆኗል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 62163 ህዳር 21 ቀን 2004 ዓ.ም. በሰጠው ገዥ ትርጉም፣ የድንጋጌው መሻር ማኅበራት ከባንክ ማበደሪያ ወለድ በላይ ማስከፈል እንደሚችሉ በመግለጽ በጉዳዩ የቀረበውን የ18% (ከመቶ) ወለድ አጽድቋል፡፡ ሆኖም ውሳኔው ፍትኃዊ አይመስልም፡፡ ሲጀምር የአዋጁ አንቀጽ 34(1) ማኅበራቱ ስለሚበደሩት እንጂ ስለሚያበድሩት ብድር የሚመለከት ባለመሆኑ፣ መሠረዙ ማኅበራቱ ስለሚያበድሩበት የወለድ መጠን በዝምታው የፍትሐ ብሔር ሕጉን የ12% (ከመቶ) ገደብ ይቀበላል፡፡ በሌላ በኩል ማኅበራት ከባንክ የማበደሪያ ወለድ መጠን በላይ እንዲያበድሩ መፍቀድ ማኅበራቱን የንግድ ማኅበራት ያደርጋቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ለትርፍ ያልተቋቋሙ መሆናቸውን ከሚገልጸው መርህ ጋር ይጋጫል፡፡

ሌላው ባህርይ አባል የሚኰንበት መንገድ ነው፡፡ በማኅበራት ውስጥ አባል ለመሆን ዕጣ ከመግዛት

ባለፈ፣ ከሌሎች አባላት ጋር የጋራ ፍላጐትና ሊፈታ የሚችል ችግር መኖር አለበት፡፡ በማኀበሩ ያለው ዕጣም ለሌላ ሰው የማይተላለፍና የሚያስገኘውም ጥቅም ዝቅተኛ ነው፡፡ በአዋጁ ማሻሻያ አንቀጽ 2(6) ማኅበሩ የካፒታል እጥረት ካልገጠመው በቀር ዕጣ የማኅበሩ አባል ላልሆነ ሰው መሸጥ አይችልም፡፡ በንግድ ማኅበራት ግን አባልነት ዕጣ ከመግዛት ጋር የሚያያዝ ሲሆን ዕጣውም ለሌሎች በሽያጭ የሚተላለፍ ይሆናል፡፡ ከዕጣ ጋር በተያያዘ ሌላው ልዩነት በማኅበራት የድምፅ አሰጣጥ የሚወሰነው በዕጣ መጠን ግምት ሳይሆን፣ የሁሉም አባል ድምፅ አንድ ብቻ ነው፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 18ን ይመለከቷል፡፡ በንግድ ማኅበራት ግን የዕጣ መጠን የድምፅ አሰጣጥን ይወስናል፡፡ የማኅበራቱ የትርፍ አደላደልም ከንግድ ማኅበራት የተለየ ነው፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 33(2) የተጣራ ትርፍ አደላደል የሚፈፀመው አባላቱ በማኅበሩ ካፒታል ውስጥ ባላቸው ዕጣ መሠረትና ለማኅበሩ ለሽያጭ ባቀረቡት ወይም በግዥ በወሰዱት ዕቃ መጠን ይሆናል፡፡ ስለዚህ ክፍፍሉ አባሉ ካለው ድርሻ ባለፈ በኅብረት ሥራ ማኅበሩ ውስጥ ባለው የግዥና ሽያጭ ተሳትፎ መሠረት ይወሰናል፡፡

የኅብረት ሥራ ማኅበራት አደረጃጀት

የኅብረት ሥራ ማኅበር አባል ለመሆን አንድ ሰው 14 ዓመት የሞላው፣ የማኅበሩን ዕጣ ለመግዛትና የመመዝገቢያ ክፍያ ለመክፈል የሚችልና የማኅበሩ ደንብና የተለያዩ አዋጆችን ለማክበር ፈቃደኛ ሊሆን ይገባል፡፡ የ14 ዓመቱ የዕድሜ ገደብ በተለይ በገጠር አካባቢ በልጅነታቸው ምርት የማምረትና ቤተሰብ የማስተዳደር ኃላፊነት ያለባቸውን ገበሬዎች ለማቀፍ መሆኑን ለመረዳት አያዳግትም፡፡ ሆኖም የዕድሜ ገደቡ በፍትሐብሔር ሕግና በቤተሰብ ሕግ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ያለውን ችሎታ ማጣት ያገናዘበ አይመስልም፡፡ አባሉ ካሉት መብቶች ለዓብነት የመበደርን መብት ብናነሳ፣ አካለ መጠን ሳያደርስ የሚወስደው/ የወሰደው ብድር በራሱ ወይስ በሞግዚቱ? በማን ይፈረማል የሚለው አከራካሪ ነው፡፡ በአንድ በኩል አዋጁ በኅብረት ሥራ ማኅበሩና በአባላቱ መካከል ለሚደረጉ ውሎች ልዩ ሁኔታ አስቀምጧል ሊባል የሚችል ሲሆን፣ በሌላ በኩል ግን የዕድሜ ገደቡ ለአባልነት እንጂ በሕግ ፊት ዋጋ ያላቸውን ጉዳዮች ለመፈፀም ረብ ስለሌለው ከማኅበሩ ተበድሮ ሲወስድ በሞግዚቱ አማካኝነት ይወከላል ልንል እንችላለን፡፡

አደረጃጀትን በተመለከተ፣ አዋጁ ከአንቀጽ 6 እስከ

12 ዝርዝር ድንጋጌዎችን አስቀምጧል፡፡ በዚህ መሠረት ማኅበራት እንደ ባህርያቸው ከመሠረታዊ እስከ ፌዴራል ደረጃ በየደረጃው መደራጀት የሚችሉ ሲሆን፣ የመሠረታዊ ማኅበር አባላት ቁጥር ከአሥር ሊያንስ አይችልም፡፡ አዋጁ ማኅበራቱ ሊመሠርቱት ስለሚችሉት የኅብረት ሥራ ኅብረት (Union)፣ ፌዴሬሽን እና ሊግ የሚለው ነገር የለም፡፡ አዋጁን ለማስፈፀም የወጣው ደንብ ቁጥር 106/1996 ዓ.ም. በዚህ ረገድ ዘርዘር ያሉ ድንጋጌዎችን ይዟል፡፡ በደንቡ አንቀጽ 5(1) መሠረት ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ኅብረቶች በፌዴራል ደረጃ ፌዴሬሽን ሊመሠርቱ እንደሚችሉ ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ ፌዴሬሽን በፌዴራል ደረጃ እንደሚመሠረት ስለሚገልጽ፣ ክልሎች ፌዴሬሽን ሊያቋቁሙ እንደማይችሉ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ሆኖም እውነታው ከዚህ የራቀ ነው፡፡ ክልሎች ፌዴሬሽን ሊያቋቁሙ የሚያስችላቸውን የሕግ ማዕቀፍ አዘጋጅተዋል፡፡ ለምሳሌ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በአዋጅ ቁጥር 154/98 አንቀጽ 8 መሠረት ፌዴሬሽን በክልሉ ሊመሠረት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ በዚህ ረገድ የሌሎች አገሮች ተሞክሮ ሁለቱንም አደረጃጀት ይደግፋል፡፡ ህንድ ውስጥ ፌዴሬሽን በክልልም ሆነ በፌዴራል ደረጃ

የሚመሠረትበት አግባብ አለ፡፡ በእኛ አገር ሕግ ግን ሕግ አውጭው ፌዴሬሽን በፌዴራል ደረጃ ብቻ ሊቋቋም እንደሚችል ያሰበ ስለመሆኑ ጸሐፊው የተመለከታቸው ጽሁፎች ስለሚያስረዱ ግጭቱ እርቅ ይፈልጋል፡፡

ሌላው ከአደረጃጀት ጋር ሊታይ የሚገባው የማኅበራት ስያሜ ነው፡፡ አዋጁ በአንቀጽ 8 ማንኛውም ማኅበር መጠሪያ ስም ሊኖረው እንደሚገባ፤ ስሙ በመጨረሻ ‹‹ኃላፊነቱ የተወሰነ የኅብረት ሥራ ማኅበር›› የሚሉ ቃላት መያዝ እንደሚገባ፤ አንድ ማኅበር በተመዘገበበት ስምና ምልክት ሌላ ማኅበር ሊጠቀምበት እንደማይችል ይደነግጋል፡፡ ‹‹ኃላፊነቱ የተወሰነ›› የሚለው ሃረግ ማኅበሩ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ እንደማይሆን ለመግለጽ ሲሆን፣ የስያሜው ልዩነትም በማኅበራት መካከል የስም አንድነት እንዳይኖር ለመከልከል ነው፡፡ በተግባር ግን በተመሳሳይ ስም የሚጠሩ ብዙ ማኅበራትን እናስተውላለን፡፡ ይህ ክፍተት በመዝጋቢው አካል የተፈጠረ ክፍተት ስለሚሆን፣ ካልተስተካከለ ትልቅ ችግር ይፈጥራል፡፡ አንዱ ማኅበር በተበደረው፣ ሌላ በተመሳሳይ ስም የሚጠራ ማኅበር እዳውን እንዲከፍል መጠየቁን

አንድ የሙያ ባልደረባዬ አጫውቶኛል፡፡

የኅብረት ሥራ ማኅበራት ዲሞክራሲያዊ በሆነ ሥርዓት እንዲመሩ የተደነገጉ አናቅጽ በአዋጁ ተካትተዋል፡፡ የማኅበራቱ የምርጫ አካሄድ፣ የኮሚቴ አወቃቀርና የቁጥጥር ሥርዓት የተወሰኑ ማሳያዎች ናቸው፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 23(2) እና 25(2) የማኅበራት የሥራ አመራር ኮሚቴና የቁጥጥር ኮሚቴ የሥራ ዘመን ሦስት ዓመታት እንደሆነና ድጋሚ ከተመረጡ ለተጨማሪ ሦስት ዓመታት ብቻ ማገልገል እንደሚችሉ ደንግጓል፡፡ አንዳንድ ጽሑፎች እንደሚያሳዩት፣ በአገራችን በሚገኙ አብዛኞቹ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ይህ ተግባራዊ አይደረግም፡፡ በሌላ በኩል የክልሎች ተሞክሮ የኮሚቴ የሥራ ዘመን የማይገደብበትን አካሄድ ያሳያል፡፡ የትግራይ ክልል ኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 145/2000 በአንቀጽ 23(2) ‹‹የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ይሆናል፤ የማኅበሩ አባላት ከመረጧቸው ግን ከዚያ በላይ ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡›› በማለት ስለሚደነግግ የኮሚቴዎችን ተጠያቂነትና የማኅበራትን ዲሞክራሲያዊ አሠራር ያፋልሳል፡፡ የኅብረት ሥራ ማኅበራቱም በተወሰኑ አመራር አካላት ቁጥጥር ሥር

በመውደቅ ወዳልተፈለገ አቅጣጫ ይሄዳሉ፡፡

የኅብረት ሥራ ማኅበራት ልዩ መብቶች

አዋጁና ማሻሻያው ለኅብረት ሥራ ማኅበራት ልዩ መብቶችን ያጎናጽፋል፡፡ እነዚህን ልዩ መብቶች በአጭሩ እንመልከት፡፡ የመጀመሪያው የማኅበራት ዕዳ በቀዳሚነት እንዲከፈል የተቀመጠው ደንብ ነው፡፡ አዋጁ በአንቀጽ 28 ‹‹በማንኛውም ሕግ በሌላ ሁኔታ የተደነገገ ቢኖርም ማንኛውም ማኅበር ከአንድ አባል ላይ የሚፈልገው የዕዳ ክፍያ የመንግሥት ዕዳን ሳይጨምር ከሌሎች ዕዳዎች ክፍያ ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡›› በሚል ይደነግጋል፡፡ ይህ የቅድሚያ መብት ወሰን በተግባር አከራካሪ ሊሆን እንደሚችል ማሰብ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ አንድ በኅብረት ሥራ ማኅበር ውስጥ ዕዳ ያለበት አባል፣ መኖሪያ ቤቱን በመያዣ በመስጠት ከባንክ ቢበደር፤ ወይም ቤቱን በገነባለት ሥራ ተቋራጭ ዕዳ ቢኖርበት፣ የኅብረት ሥራ ማኅበሩ፣ በአባሉ ቤት ላይ ከባንኩ ወይም ከሥራ ተቋራጩ ቅድሚያ ሊከፈለው ይገባል ወይስ የባንኩ የመያዣ መብት (የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 3059) ወይም የሥራ ተቋራጩ የቅድሚያ መብት (የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር

3067) ይቀድማል? የአዋጁ ድንጋጌ የኅብረት ሥራ ማኅበሩን ከመንግሥት ቀጥሎ የሚያስቀድም ሲሆን፣ የፍትሐ ብሔር ሕጉ የመያዣ መብት ድንጋጌዎች ደግሞ የኅብረት ሥራ ማኅበሩን መብት ቅድሚያ አይሰጥም፡፡ ስለዚህ በቀዳሚነት መብት ረገድ የአተረጓጎም ልዩነት መፈጠሩ አይቀርም፡፡ የአዋጁ ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው ማኅበሩም ሆነ ሌሎች ባለገንዘቦች (ባንኮች) ተራ ተበዳሪ (unsecured creditors) በሆኑበት ጊዜ እንደሆነ ካሰብን ግን ተቃርኖ አይኖርም፡፡

ሁለተኛው የኅብረት ሥራ ማኅበራት የአባላትን ዕጣ ወይም ጥቅም የማቻቻል መብት ነው፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 29 መሠረት ‹‹የማንኛውም አባል ዕጣ ወይም ጥቅም ማኅበሩ ለሚፈልግበት የዕዳ ክፍያ ማቻቻያ ሊደረግ ይችላል›› ስለሚል ለማኅበራት ከሕግ የመነጨ የማቻቻል መብት ያጎናጽፋቸዋል፡፡ ከማቻቻል ባለፈ በአንቀጽ 30 መሠረት፣ አባሉ በማኅበሩ ውስጥ ያለው ዕጣ ወይም ጥቅም አባሉ ላለበት ዕዳ ማስከፈያ ሲባል ሊከበር ወይም ሊሸጥ አይችልም፡፡ ይህ ድንጋጌ የሦስተኛ ወገን ባለገንዘቦችን መብት የሚያጣብብ ቢመስልም፣ የኅብረት ሥራ ማኅበራት መርሆችን ለመፈፀም

ያስችላል፡፡ የአባላትን የጋራ ማኅበራዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ችግር ለመፍታት በማሰብ ያሰባሰቡትን ገንዘብ ከሦስተኛ ወገን በመጠበቅ የተነሱበትን ዓላማ እንዲያስፈጽሙ ሕጉ እገዛ ያደርጋል፡፡

ሦስተኛው የኀብረት ሥራ ማኅበራት በመንግሥት የሚሰጧቸው ልዩ ልዩ ድጋፎች ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ ማኅበራት ከሚያገኙት ገቢ ከገቢ ግብር ነፃ ናቸው፤ መሬትም የማግኘት መብት ይኖራቸዋል (አንቀጽ 31)፡፡ ሆኖም አባላት ከሚያገኙት የዕጣ ድርሻ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የገቢ ግብር የሚከፍሉ ሲሆን፣ ማኅበሩም መሬት የሚያገኘው ከሊዝ ነፃ ይሁን በሊዝ ቅድሚያ ተሰጥቶት ግልጽ አይደለም፡፡ ከግብር ነፃ መብቱ ማኅበራቱ ከገቢያቸው የሚከፍሉትን ግብር እንጂ በሌላ የግብር አይነቶች መክፈል ያለባቸውን ግዴታ አይጨምርም፡፡ ለዓብነት ማኅበራቱ በአዋጅ ቁጥር 110/90 መሠረት የቴምብር ቀረጥ የመክፈል ግዴታቸውን የሚያስቀር አይሆንም፡፡

አራተኛው በማሻሻያው የተጨመሩ ልዩ መብቶች (privileges) ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ ማኅበራት ከተመዘገቡበት ጊዜ ጀምሮ ተጨማሪ የንግድ ፈቃድ

ሳያስፈልጋቸው በማንኛውም የንግድ ሥራ ላይ መሰማራት ይችላሉ፤ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ካወጣ ከንብረታቸው ጋር በተያያዘ በፍ/ቤት ላለባቸው ክርክሮች ከሚከፈል የዳኝነት ክፍያ ነፃ ለሆኑ ይችላሉ፤ እንዲሁም ከንብረት ጋር በተያያዘ ማኅበራት ከሚፈጽሙት ውል የሚመነጭ መብት ከ20 ዓመት በኋላ ቀሪ ይሆናል፡፡ የንግድ ፈቃዱ ልዩ መብት አከራካሪ ነው፡፡ መብቱ ንግድን ያለንግድ ፈቃድ ለማከናወን የሚፈቅድ በመሆኑና ማኅበራቱ ከሚሠሩት ሥራ ውጭ ባሉ የንግድ ሥራዎችም ተፈፃሚ ስለሚሆን፣ የንግድ ውድድርን ትርጉም ያሳጣል፡፡ ማኅበራቱም ከተቋቋሙበት ዓላማና ከመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበራት መርሆች እንዲወጡ ፈተና ሊሆንባቸው ይችላል፡፡

ከዳኝነት ክፍያ ነፃ የመሆን መብት በቅድመ ሁኔታ የታጠረ በመሆኑ፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ባልወጣበት ሁኔታ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡ ሆኖም በአንዳንድ ክልሎች ግልጽ ደንብ የወጣ በመሆኑ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ከዳኝነት ክፍያ ነፃ መብት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ሌላው ማሻሻያው የይርጋ ደንብን በፍትሐ ብሔር ጉዳይ ተግባራዊ ከሆነው የአሥር ዓመት ገደብ ረዘም ያለ ጊዜ አስቀምጧል፡፡

በማሻሻያው የተቀመጠው የ20 ዓመት ይርጋ፣ ማኅበራቱ በሚፈጽሙት ውልም ተፈፃሚ ስለሚሆን ያበደሩትን ዕዳ ለማስመለስ የተሻለ የይርጋ ደንብ ተቀምጧል፡፡ ማኅበሩ በተበደረበት ሁኔታም ይርጋው ተፈጻሚ ስለሚሆን፣ ከማኅበሩ ጋር ለሚዋዋሉም ሰዎች ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ከይርጋ ደንብ ጽንሰ ሐሳብ የራቀ ድንጋጌ የተቀመጠው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 134/1998 ነው፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 34 ‹‹የይርጋ ጊዜን አስመልክቶ በሌላ ሕግ የተደነገገው ቢኖርም አንድ ማኅበር ጊዜው ያለፈበትን ዕዳ ከአባላቱ ወይም ከአቻ ማኅበራት ላይ በማናቸውም ጊዜ ለመጠየቅ የይርጋ ሥነ ሥርዓት አያግደውም፡፡›› በማለት የማኅበራት ዕዳ በይርጋ እንደማይታገድ ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ ዓላማው ከአዋጁ በፊት በማኅበራት ተሰጥተው ያልተሰበሰቡ ዕዳዎችን ማኅበራት እንዲሰበሰቡ ማስቻል ነው፡፡ የድንጋጌው የተፈፃሚነት ወሰን በማኅበሩና በአባላት ወይም በአቻ ማኅበራት መካከል ያለው የውል ግንኙነት ላይ ስለሆነ ከሌሎች ተዋዋይ ወገኖች ጋር ተፈፃሚ ሊሆን እንደማይችል መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል በአባላትና በአቻ ማኅበራት ላይም

ከ1998 ዓ.ም. በፊት ለተሰጡ ዕዳዎች ተፈፃሚ ስለመሆኑ አከራካሪ ነው፡፡ በአንድ በኩል የአዋጁ አንቀጽ 67፣ አዋጁ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ በኋላ ተፈፃሚ ስለመሆኑ የሚደነግግ ሲሆን፣ ወደ ኋላ እንዲሠራ ማድረግም ከሕግ መርህ አንፃር ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ የይርጋ ደንቡ ከአዋጁ መውጣት በፊትም ተፈፃሚ ይሆናል ከተባለ፣ ይርጋው በጊዜ ገደብ አለመወሰኑ የይርጋውን ጽንሰ ሃሳብ ትርጉም ያሳጣዋል፡፡ ይርጋ አንድ መብት በሕግ የሚጠይቅበትን የጊዜ ወሰን የሚገድብ በመሆኑ ልቅ የሚተው አይሆንም፡፡ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1206 ከተደነገገው የመፋለም መብት ውጭ የፍትሐ በሔር መብቶች በአገራችን የጊዜ ወሰኑ በተቆረጠለት የይርጋ ደንብ ይገዛሉ፡፡ ስለዚህ የአማራ ክልሉ አዋጅ ጊዜው ቢበዛም ይርጋውን በጊዜ ወስኖ ሊያስቀምጥ ይገባ ነበር፡፡ የይርጋ ደንቡ አባላት/አቻ ማኅበራት ለዘለዓለም እንዲበረግጉ፤ ማኅበሩም መብቱ ላይ እንዲተኛ የሕግ መሠረት ይሰጣል፡፡

## የኅብረት ሥራ ማኅበራት ክርክር አወሳሰን

አዋጁ በኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚነሱ አለመግባባቶችን በሽምግልና ዳኝነት ለመፍታት

የሚያስችል አሠራርም ዘርግቷል፡፡ ሆኖም በአዋጁ የተቀመጠው ድንጋጌ ግልጽነት ይጎድለዋል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 49 ስለአንድ ማኅበር አቋም፣ ስለ ሥራው አካሄድ ወይም ስለ ሥራው አፈፃፀም በተመለከተ በማኅበሩና በአባላት፣ በቀድሞ አባላት፣ ወኪሎች፣ ወራሾች፣ ሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም በሌላ ማኅበር መካከል በዕርቅ ያላለቁ ጉዳዮች በሽምግልና ዳኞች እንደሚታዩ ይደነግጋል፡፡ የሽምግልና ዳኞቹ የፍትሐ ብሔር ችሎት ሥልጣን ያላቸው ሲሆን የሚሰጡት ውሳኔ አስፈላጊ ሲሆን በፍ/ቤቶች ሊፈፀም ይችላል፡፡

በሽምግልና ዳኞች ውሳኔ ይግባኝ የሚጠየቀው ለፌዴራል ወይም ለክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሆኑን የአዋጁ አንቀጽ 52 ይደነግጋል፡፡ አከራካሪው ነጥብ ማኅበራቱ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር ያላቸው ክርክር ወይም አባላት በአዋጁ አንቀጽ 39(3) መሠረት ከጉድለት ገንዘብ ጋር በተገናኘ የሚነሱ ክርክሮች ቀጥታ ወደ ፍርድ ቤቶች ሊሄዱ ስለመቻል አለመቻላቸው ነው፡፡ በተግባር አንዳንድ ፍርድ ቤቶች ማኅበራት ከሦስተኛ ወገኖች ጋር ያላቸው ክርክር እና በአንቀጽ 49 ባልተገለጹ ጉዳዮች ከአባላት ጋር ያላቸው ክርክር ወደ ፍርድ

ቤት ሊሄዱ ይችላሉ በሚል አቋም የያዙ ሲሆን ሌሎች ደግሞ ሁሉም ጉዳዮች ቅድሚያ በእርቅና በሽምግልና ዳኝነት ሳይታዩ ወደ ፍርድ ቤት ሊቀርቡ አይገባም ይላሉ፡፡ ጸሐፊው ከአንቀጽ 49 የመግቢያ ኃይለ ቃሎች በመነሳት ሕግ አውጭው ሁሉም ጉዳዮች ወደ ሽምግልና ዳኝነት እንዲሄዱ ፍላጐት ያለው አይመስለውም፡፡

ከአዘጋጁ፡- ጸሐፊው የሕግ ጠበቃና አማካሪ ሲሆኑ፣ በኢሜይል አድራሻቸው getukow@gmail.com ማግኘት ይቻላል፡፡